ከሜሪላንድ የኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት መመዘኛዎች ጋር የሚጣጣሙ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ እና ሂሳብ የሜሪላንድ አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም (MCAP) ግምገማዎች በ2021-2022 የትምህርት ዓመት ተሰጥተዋል። እነዚህ ምዘናዎች የልጅዎን የትምህርት አፈጻጸም በሚመለከት ከሚደረጉ ምዘናዎች አንድ መለኪያ ብቻ ነው። ከምዘናዎቹ የተገኙ ውጤቶች ለልጅዎ መምህር፣ ለት/ቤት እና ለትምህርት ስርዓቱ ተቋም ስለአካዳሚክ ውጤቶቹ መረጃ የሚሰጡ ሲሆን ስለልጅዎ የትምህርት ብቃት ደረጃ የተወሰነ ግንዛቤ ይሰጡዎታል። ተማሪ የአካዳሚክ ደረጃዎችን ለማሟላት የሚያደርገውን/የምታደርገውን እድገት ግልፅ ለማድረግ MCAP ውጤቶች ከተማሪው(ዋ) የትምህርት ክፍል አፈጻጸም፣ የሪፖርት ካርድ ውጤቶች እና የአስተማሪ ግብረመልስ ጋር አብሮ መታየትና ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

## የእርስዎን ተማሪ የውጤት ሪፖርት እንዴት እንደሚያነቡ

1. **አጠቃላይ ክንውን/Overall Performance**–ተማሪዎች አጠቃላይ ውጤት የሚያገኙት ከአራቱ የትምህርት አፈጻፀም ደረጃዎች በአንዱ ላይ በሚመደበው በእያንዳንዱ የትምህርት አይነት ተመስርቶ ነው። የአፈጻጸም ደረጃዎች፡ ተማሪ ገና የብቃት ደረጃን እንዳላሳየ(ች) ከሚያመለክተው ከደረጃ 1 እስከ የክፍል ደረጃ መመዘኛዎችን የላቀ ብቃት እንዳሳየ(ች) የሚያመለክት ደረጃ 4 ድረስ ይለያያሉ።

2. **የውጤት ደረጃዎች/Score Range** – ይህ ሚዛን የእያንዳንዱን ክንውን የውጤት ደረጃ እና የእርስዎ ተማሪ ከእነዚህ መካከል በየትኛው ደረጃ እንደሚገኝ/እንደምትገኝ ያመለክታል።

3. **ለኮሌጅ እና የሙያ ሥራ ዝግጁ/On Track for College and Career**– 3 ወይም 4 ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን የክፍል ደረጃ አሟልተዋል ወይም ከማሟላትም የሚበልጥ ስለሆነ ከሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንደተመረቁ የኮሌጅ ደረጃ ኮርስ ለመውሰድ ዝግጁ ናቸው።

4. **አጠቃላይ የነጥብ/ዉጤት ማነፃፀሪያዎች/Overall Score Comparisons**–ይሄኛው ክፍል የሚያመለክተው በተመሣሣይ የክፍል ደረጃ፣ በተመሣሣይ ት/ቤት፣ በትምህርት ዲስትሪክቱ በአጠቃላይ፣ እና በስቴቱ ከሌሎች ት/ቤት ተማሪዎች ጋር ሲነጻፀር የእርስዎ ልጅ እንዴት እያከናወነ(ች) እንደሆነ ያመለክታል።



# የተማሪዎን የውጤት ሪፖርት እንዴት እንደሚያነቡ (የቀጠለ.)

5. **የማንበብ/የመጻፍ ክንዋኔ - Reading/Writing Performance–** የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ ሪፖርት የእርስዎን ተማሪ የማንበብ እና የመጻፍ ነጥቦችን ያነፃጽራል። በዚህ ንዑስ ክፍል በሚገኙ ጥያቄዎች ተማሪዎ ያስመዘገበ(ች)ውን ውጤት በቁጥር ያመለክታል። ለማመሳከር እንዲረዳዎት ተማሪዎ ካገኘ(ች)ው ውጤት በተጨማሪ "ከ-እስከ" የውጤት እርከን ደረጃ ተገልጿል። ይህኛው ን/ክፍል በተጨማሪ የት/ቤቱን፣ የዲስትሪክቱን፣ እና የስቴቱን አማካይ ውጤቶች ያካትታል።

6. **የውጤት ዝርዝር/Score Breakdown–** የውጤት ሪፖርት በተወሰነ የክህሎት ደረጃ የእርስዎ ልጅ እያቀላጠፈ(ች) ያለውን ወይም ማሻሻል ያለበ(ባ)ትን የተማሪ አፈጻጸም ዝርዝር ያመለክታል። እያንዳንዱ ዝርዝር የሚጠበቅባቸውን ካሟሉ ተማሪዎች ጋር የእርስዎን ተማሪ አፈጻጸም የሚያሣይ ክብ ማነጻፀሪያ ያካትታል። የሚማርበትን/የምትማርበትን ክፍል የብቃት/የክሂሎት ግንዛቤ ደረጃ የሚገልጽ ውጤት-የሚያሳይ ገለፃም በተጨማሪ ተካትቷል።







## ስለ ሜሪላንድ ምዘና እና የፈተና አሰጣጥ እውነታዎች

- ✓ ከ3ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከገቡ በኋላ ዓመታዊ የስቴት አቀፍ መመዘኛ እንዲወስዱ የፌደራል ህግ ይደነግጋል።
- ✓ የሜሪላንድ የትምህርት ባለሙያዎች ከትንታኔ አንስቶ ትክክለኛነታቸውን እስከ መገምገም ድረስ እያንዳንዱን ፈተናዎችን በማዘጋጀት እና በማሻሻል ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ።
- ✓ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎች ሊፈቀድላቸው ስለሚችል መገልገያዎች እና አኮሞዴሽን ለመወያየት በልጆቻቸው IEP ወይም 504 ቡድን አማካይነት ለወላጆቻቸው ሊገለጽላቸዉ ይገባል።
- ✓ ውጤቶች በትምህርት አመቱ መጨረሻ የተማሪን የክፍል ደረጃ ትምህርት የግንዛቤ ደረጃን ያሳያሉ።
- ✓ የውጤት ሪፖርቶች የሚያገለግሎት:- መመህራን የዳበረ የማስተማር እቅድ አዘጋጅተው ተማሪዎችን ለመጪው የትምህርት ዓመት የሚቀጥለውን እርከን እቅድ ለማዘጋጀት የሚረዱ መሳርያዎች ናቸው።
- ✓ ቤተሰቦች ስለልጃቸው አካዴሚያዊ ጥንካሬና መሻሻል ስላለበት ሁኔታ ከልጃቸው መምህራንና የት/ቤት ሃላፊዎች ጋር ውይይት ለማድረግ እነዚህን ውጤቶች መጠቀም ይችላሉ።
- ✓ በት/ቤትም ሆነ በመኖርያ ቤት የተማሪው(ዋ)ን የትምህርት ፍላጎት በይበልጥ እንዴት መደገፍ እንደሚቻል እያንዳንዱን ጉዳይ አብሮ መወሰን ይቻላል።

## አጋዥ ድረ-ገጾች

- ✓ **MCAP የመልመጃ ፈተናዎች** - support.mdassessments.com
- ✓ **Achieve –** Resources on Standards – achieve.org
- ✓ **MDK12 –** mdk12.msde.maryland.gov
- ✓ **Great Kids –** greatschools.org/gk/common-core-test-guide
- ✓ **Be a Learning Hero –** bealearninghero.org/learning-tools/skill-builder